# ድርቅና ርሃብ ተፋትተዋል!

ኢብሳ ነመራ

ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በድርቅ ስትመታ የኖረች ገር ነች። እርግጥ ድርቅ የተፈጥሮ አደጋ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ብቻ የታዘዘና በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሲደርስ የኖረ አይደለም። የበለጸጉ አገራትን ጨምሮ በርካታ የዓለም አካባቢ ያጋጥማል። ለምሳሌ፤- በ2007 ዓ.ም ኤልኒኖ በተሰኘው የአየር ንብረት መዛባት ክስተት የተፈጠረው ድርቅ ባለጸጋዋን አሜሪካን ጭምር አልማረም። የአሜሪካ ካልፎርኒያ ግዛት በታሪኩ አስከፊ በተባለ ድርቅ ተመትቷል። ድርቅ በተለይ በግብርና ዘርፍ ላይ በሚያሳድረው አሉታዊ ጫና ጉዳት ማድረሱ አይቀሬ ቢሆንም፤ አስከፊ የሚሆነው ግን ርሀብ አስከትሎ ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሲሆን ነው። ቸነፈር አስከትሎ ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሚሆነው ተጽአኖውን መቋቋም የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም ሳይኖር እና/ወይም የህዝብ ውክልና ያለው መንግስት ሳይኖር ቀርቶ የድርቁ ተጽእኖ ይፋ ሳይወጣ ሲቀር ነው።

ኢትዮጵያ በይፋ ከሚታወቀው በ1880ዎቹ ካጋጠማት ክፉ ቀን በመባል ከሚታወቀው ድርቅ ጀምሮ ቢያንስ በየ10 ዓመቱ በድርቅ ስትመታ ቆይታለች። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት የጠፋበት የ1965/66፤ እንዲሁም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት የጠፋበት የ1976/77 ድርቅ ያስከተለው ረሃብ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ድርቅ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያን አልለቀቀም። ይሁን እንጂ፤ ድርቅ ወደርሀብነት ተለውጦ የዜጎችን ህይወት የሚቀጥፍበትን ሁኔታ መቀየር ተችሏል። ድርቅ የተፈጥሮ ክስተት በመሆኑ እስካሁን ባለው የሰው ልጅ ስልጣኔ እንዳይደርስ ማድረግ አልተቻለም። የተቻለው ድርቅ ርሀብ ሆኖ ሰው እንዳይገል ማድረግ ነው።

በዚህ ረገድ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ስኬታማ ስራ መስራት ተችሏል። ከወታደራዊው ደርግ ውድቀት በኋላ በ1989፤ በ1994/95፤ በ2003 ዓ.ም ድርቅ ተከስቷል። በተለይ በ1994/95 ዓ.ም ተከስቶ የነበረው ድርቅ 14 ሚሊዮን ያህል ዜጎች ለምግብ እጥረት የተጋለጡበት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። በእነዚህ ዓመታት በተለይ በ1989 ዓ.ም እና 1994/95 ዓ.ም አገሪቱ ደርቅ ያስከተለውን የምግብ እጥረት ተጽእኖ በራስዋ አቅም መመከት የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም አልነበራትም። በእነዚህ ዓመታት ድርቅ ያስከተለው የምግብ እጥረት ለዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሳይሆን መከላከል የተቻለው በ1965/66 እና በ1976/77 ከነበረው በተለየ ሁኔታ መንግስት ችግሩ እንደታየ  ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳወቅ ሳይረፍድ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ በመገኘቱ ነው። የድርቅን ተጽእኖ ለመቋቋም ከሚያስቸልው አንዱ ጉዳይ በህዝብ ውክልና የተሰጠው ዴሞክራሲያዊ ስርአት መኖር ነው። ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ የዴሞክራሲ አንዱ መገለጫ በሆነው ህዝባዊ ጉዳዮችን ግልጽ ማድረግ መርህ መሰረት ድርቅ እንደተከሰተ ችግሩን ለዜጎችና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳወቅ ርሀብን መከላከል ተቸሏል።

በ2004 ዓ.ም በተለይ ምስራቅ አፍሪካን የመታውና በኢትዮጵያ ምስራቃዊና ደቡብ ምስራቃዊ አካባቢዎች የተከሰተውን አሰከፊ ድርቅ መከላከል ያስቻለው የመንግስት ግልጽነትና ቀደም ሲል ከነበረው የጠነከረ አገራዊ የኢኮኖሚ አቅም መኖር ነው። በወቅቱ ድርቁ የምግብ እጥረት ማስከተል ሲጀምር ከዚያ ቀደም ከነበሩት ድርቆች ሁሉ በተለየ ሁኔታ መንግስት ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የሚውል የመጠባበቂያ የእህል ክምችት ስለነበረው ችግሩን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አሳውቆ የተጠየቀው እርዳታ እስኪደርስ ከመጠባባቂያ ክምችቱ እርዳታ በማቅረብ ነበር መከላከል የተቻለው።

በ2007 ድርቅ ሳቢያ የተከሰተውን የምግብ እጥረት አገሪቱ የተቋቋመችበት ሁኔታ ደግሞ ከ2004ቱም የተለየ ነበር። ይህም የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታው በከፊል በራስ አቅም የተሰጠ መሆኑ ነው። በእርዳታ መስጫ ጣቢያዎች የለጋሽ አገራትንና ድርጅቶችን አርማ ከያዙ የእርዳታ እህል ከረጢቶች ጎን የኢትዮጵያን መንግስት አርማና ሰንደቅ ዓላማ የያዙ ከረጢቶችም ተሰልፈው ነበር። ይህ በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያው ነው። አገሪቱ ለዚህ የበቃችው ከዚያ ቀደም በነበሩት አስራ ሁለት ዓመታት ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገቧና የድርቅን ተጽእኖ መቋቋም የሚችል አቅም በመገንባቷ ነው። መንግስት በድርቁ ምክንያት የአንድም ሰው ህይወት አይጠፋም፤ የውጭ እርዳታ ባናገኝ እንኳን ግዙፍ ፕሮጀክቶቻችንን ለጊዜው ገታ አድርገን በጀታችንን በማጠፍ ዜጎቻችን እንታደጋለን የሚል አቋም ይዞ ይፋ ያደረገው ድርቁ እንደተከሰተ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ከተከሰቱት ሁሉ አስከፊ የተባለውን ድርቅ ለመቋቋም በወሰደው እርምጃ ያለፈበትን ሂደት መለስ ብለን እናስታውስ።

የድርቁን ተፅእኖ የመከላከል ተግባር ባለፉት ድርቅ የተከሰተባቸው ጊዜያት ከተደረገው ሁሉ በተለየ ሁኔታ በኢትዮጵያ መንግስት ግንባር ቀደምትነት በፌደራልና በክልል ደረጃ የአደጋ መከላከል አቢይ ኮሚቴዎችን፤ እንዲሁም የቴክኒክ ኮሚቴዎችን በማዋቀር በተቀናጀ ሁኔታ የተከናወነ ነበር።

እንደሚታወሰው የኢትዮጵያ መንግስት የበልግ ምርት ከሚሰበሰብበት የ2007 ዓ.ም ሰኔ ወር ማብቂያ ጀምሮ ነበር በድርቁ ምክንያት የምግብ እጥረት ማጋጠሙን ይፋ ያደረገው፤ ብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የምግብ እጥረት ተጋላጮችን ቁጥር በየወቅቱ ይፋ ሲያደርግ ቆይቷል። ይህ የምግብ እጥረት ተጋላጮችን ቁጥር በትክክል የመለየትና ይፋ የማድረግ ተግባር የእርዳታ አቅርቦቱን ከእርዳታ ፈላጊው ጋር ማመጣጠን አስችሏል።

ኮሚሽኑ በየወቅቱ ይፋ ሲያደርገው በነበረው መረጃ መሰረት፤ በበልግ ዝናብ መዛባት ሳቢያ ሰኔ 2007 ዓ.ም ላይ ለምግብ እጥረት የተጋለጡት ዜጎች ቁጥር 2 ነጥብ 9 ሚሊዮን ነበር። ከ2007 በልግ በተጨማሪ፤ የክረምቱ ዝናብ መቆራረጥና መቆም በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት የተጋለጡና የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር በሰኔ ወር ከነበረበት 2 ነጥብ 9 ሚሊዮን በነሃሴ ወር ወደ 4 ነጥብ 3 ሚሊዮን ከፍ አድርጎታል። ጥቅምት 2008 መግቢያ ላይ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ፈላጊዎቹ ቁጥር 8 ነጥብ 2 ደረሰ፤ ታህሳስ 2008 ላይ ይፋ በተደረገው መረጃ መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ፈላጊዎች ቁጥር 10 ነጥብ 241 ሚሊዮን ደረሰ። በነሃሴ ወር ይህ ቁጥር በ500 ሺህ ቀንሶ 9 ነጥብ 741 ሚሊዮን ሆነ፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ፈላጊዎች ቁጥር የቀነሰው በበልግ ዝናብ መስተካካል የተነሳ ነበር። ይህ ያለፈው ዓመት የተረጂዎች ቁጥር የመኸር ምርት ተሰብስቦ እስከሚገባበት ቀጣይ ወር ድረስ ይቀጥላል ተብሎ ይጠበቃል።

የኢፌዴሪ መንግስት በድርቁ ምክንያት የምግብ እጥረት ለገጠማቸውና የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለሚፈለጉ ዜጎች እርዳታ ማቅረብ የጀመረው ከሰኔ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ነበር። በተለይ የትራንስፖርትና የመገናኛ መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ባልተስፋፋባቸው ራቅ ያሉ የአፋርና የሶማሌ አካባቢዎች በግጦሽ ሳርና በውሃ እጥረት ከብቶች የሞቱበት ሁኔታ ስለነበረ ይህን ለመከላከል የፌደራል መንግስት ከክልሎቹ ጋር በመቀናጀት መኖና ውሃ በማቅረብ ከብቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የመከላከል ስራ አከናውኗል።

ድርቁ የምግብ እጥረት ማስከተል በጀመረበት ወቅት ለአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ የሚውል ለአጣዳፊ የምግብ አቅርቦት ሊውል የተዘጋጀ የመጠባበቂያ የእህል ክምችት ነበር። የምግብ እጥረቱ በተከሰተበት ከሰኔ 2007 ዓ.ም ላይ 451 ሺህ ሜትሪክ ቶን (4 ሚሊዮን 451 ሺህ ኩንታል) የመጠባበቂያ የዕህል ክምችት ነበር።

በሌላ በኩል፤ በኢኮኖሚ እድገቱ ምክንያት የመንግስት ገቢ በመጨመሩ መንግስት ለእርዳታ ተግባር የሚውል በጀት የመመደብ አቅምም ፈጥሯል። በመሆኑም መንግስት ድርቁ ያስከተለውን የምግብ እጥረት ለመከላከል ባለፈው ዓመት የ18 ቢሊዮን ብር በጀት ይዟል። በዚህ ለእርዳታ አቅርቦት በተመደበ ገንዘብ ከውጭ በሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚለካ እህል ተሸምቷል።

መንግስት የድርቁን ተፅእኖ ለመከላከል የእርሻና ተዛማጅ ስራ ድጋፍ ከማድረግ፤ እንዲሁም በቀጥታ ለአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የምግብ ድጋፍ ከማቅረብ በተጨማሪ በድርቁ ምክንያት የጤና ችግርና የትምህርት መስተጓጎል ችግር ለተጋለጡ ዜጎች ድጋፍ መደረጉን የብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን መረጃ ያመለክታል። በዚህ መረጃ መሰረት፤ በጤናው ዘርፍ የስርአተ ምግብ ችግር ለመከላከል በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ህፃናት የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል። የወባ፤ የኩፊኝ፤ የአደገኛ ተላላፊ ተቅማጥ፤ የማጅራት ገትር፤ የገንዲ፤ የትክትክና የመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ክትባት የመስጠትና አጎበር የማደል ስራ ተከናውኗል።

በውሃ ዘርፍ ለሰውና ለእንስሳት የአስቸኳይ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለማሻሻል የውሃ ተቋማት ጠረጋና እድሳት፤ የውሃ ጉደጓድ ቁፋሮ፤ የቁሳቁስ አቅርቦትና ስርጭት ስራ ተከናውኗል። በዚህም ጠላቂ ፓምፕ፤ ጄኔሬተር፤ የውሃ ማጣሪያና ማከሚያ፤ የእጅ ፓምፕ፤ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ለሙያና ተያያዥ ጉዳዮች የ81 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል።

ከትምህርት ጋር በተያያዘ፤ ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ተማሪዎች ለችግር ተጋልጠዋል። ለእነዚህ ተማሪዎች የትምህርት መሳሪያዎች፤ ምግብና ውሃ የማቅረብ አገልግሎት ተሰጥቷል። በሌላ በኩል፤ ተማሪዎች በድርቁ ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይስተጓጎሉ ከ6 መቶ ሚሊዮን ብር በላይ በጀት በመመደብ የትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራም ተከናውኗል። በዚህም 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት በመቻሏ የድርቁን ተጽእኖ ለአንድም ሰው ህይወት መጥፋትና ከመኖሪያ ቀዬ መፈናቀል ምክንያት ሳይሆን መከላከል ችላለች። እርግጥ ድርቁ በአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ላይ መጠነኛ ተጽእኖ አሳድሯል። የባለፈው ዓመት የኢኮኖሚ እድገት ቀደም ሲል ከነበረው አማካይ ባለሁለት አሃዝ እድገት ወደ 8 በመቶ ዝቅ ብሏል። ይህም ቢሆን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ነው። አገሪቱ የድርቁን ተጽእኖ በመቋቋም ፈጣን ኢኮኖሚ ማስመዝገብ የቻለችው በቀደሙት ዓመታት እድገት ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባቷ ነው።

በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዘመን በዓመት በአማካይ 6 ነጥብ 6 በመቶ ዕድገት ሲያስመዘግብ የቆየው የግብርናው ዘርፍ ባለፈው ዓመት ኤልኒኖ ባስከተለው ድርቅ ምክንያት እድገቱ ወደ በ2 ነጥብ 3 በመቶ ዝቅ ቢልም አጠቃላይ ኢኮኖሚው ግን እድገት ማሳየቱ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከግብርና ጥገኝነት እየተላቀቀ መሆኑን ያመለክታል። ባለፈው ዓመት ኢንዱስትሪ በ20 ነጥብ 6 በመቶ፤ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ በ8 ነጥብ 7 በመቶ እድገት ማሳየቱን ከብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 44 ነጥብ 4 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 36 ነጥብ 4 ዝቅ ብሏል። በሌላ በኩል፤ በተመሳሳይ ጊዜ ኢንዱስትሪው በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከ10 ነጥብ 4 በመቶ ወደ 16 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ ብሏል። የአገልግሎት ዘርፉ ደግሞ፤ ከነበረበት 45 ነጥብ 2 በመቶ ወደ 47 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህ

በአጠቃላይ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ከመመዝገቡ በተጨማሪ የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ ወይም ሽግግር የማምጣቱ እቅድ የስኬት አቅጣጫ መያዙን ያመለክታል።

ለባለፈው ዓመት የኢኮኖሚ እድገት መቀነስ ምክንያት የነበረው የግብርናው ዘርፍ ዘንድሮ በከፍተኛ መጠን እድገት አሳይቷል። ዘንድሮ 320 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይሰበሰባል ተብሎ ይጠበቃል። በመሆኑም የአገሪቱ እድገት በታቀደው መሰረት ቢያንስ በ11 በመቶ ማደግ እንደሚችል ተገምቷል።

ከላይ እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እየጠነከረ በመምጣቱ ድርቅ የሚያስከትለውን የምግብ እጥረት ተጽእኖ መከላከል ከመቻሉ በተጨማሪ፤ ድርቁ በግብርና ምርት ላይ ጉልህ ተፅእኖም አሳድሮ በነበረበት ሁኔታም እንኳን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የተቻለበት አቅም ተፈጥሯል።

በባለፈውም ክረምት የሰው ልጅ እስካሁን ባለው ስልጣኔው ሊቋቋመው ያልቻለው ድርቅ የተወሰኑ የአገሪቱን አካባቢዎች በተለይ ምስራቃዊውን እና ደቡብ ምስራቃዊውን አካባቢ መትቷል። የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ስራ አስኪያጅ አቶ ምትኩ ካሳ ከሁለት ሳምንት በፊት ከኢቢሲ ጋር በነበራቸው ቆይታ 2 ሚሊዮን ያህል ሰዎች ለድርቅ ተፅእኖ መጋለጣቸውንና ይህም አስቀድሞ የተተነበየና ዝግጅት የተደረገበት በመሆኑ ጉዳት እንደማያስከትል አስታውቀዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትም በክልሉ ባሉ ድርቁ ያረፈባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች በተለይ የከብት መኖ ማቅረብ መጀመሩን መረጃዎች ያመለክታሉ።

እዚህ ላይ ዋናው ነገር ድርቅ መከሰቱ አይደለም። ድርቅ የትም አገር በበለጸጉት አገራትም ጭምር ይከሰታል። ድርቅ የመንግስት ፖሊሲና የአፈጻጸም ውጤት ሳይሆን የተፈጥሮ ክስተት በመሆኑ፤ ዋናው ነገር መንግስት የድርቅን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያስችል ግልጽነትና እርዳታ ማቅረብ የሚያስችል ስርአትና የኢኮኖሚ አቅም አለው ወይ? የሚለው ነው። በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ መንግስት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግልጽነትና እርዳታ ማቅረብ የሚያስችል ስርአት፤ እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም አለው። ይሁን እንጂ፤ አንዳንድ ወገኖች ይህን ድርቅ የፖለቲካ አጀንዳ ሊያደርጉት ሞክረዋል። ጉዳዩ የፖለቲካ ተቃውሞ አጀንዳ ሊሆን ይችል የነበረው መንግስት የድርቅን ተጽእኖ መከላከል የሚያስችል ፖሊሲ፣ አሰራርና የኢኮኖሚ አቅም ባይኖረው ነበር። በተለይ ባለፈው ዓመት የተከሰተው አስከፊ ድርቅ የመንግስትን አቅምና አሰራር በተግባር አረጋግጧል። አሁን መንግስት በዚህ አቅም የሚሞገስበት እንጂ የሚወቀሰበት ደረጃ ላይ አይደለም። አሁን በኢትዮጵያ ድርቅና ረሃብ ተፋትተዋል።